# ኮሎምቢያ ዲስትሪክት (DISTRICT OF COLUMBIA)
# የአስተዳደራዊ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢሮ (OFFICE OF ADMINISTRATIVE HEARINGS)

One Judiciary Square
441 Fourth Street, NW Suite 450N
Washington, DC 20001-2714
ስልክ፣ (202) 442-9094
oah.filing@dc.gov

## ትእዛዝ

እንደ አስተዳደራዊ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢሮ (OAH ) ዋና የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ተወካይ፣ በ2001 አስተዳደራዊ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢሮ ማቋቋሚያ ህግ ክፍል 8(a)(7) እና 8(b)(12)፣ ከማርች 6፣ 2002 ጀምሮ ተፈጻሚ ከሚሆነው፣ ( D.C. ህግ 14-76፣ D.C. ኦፊሴሊያዊ ኮድ § 2-1831.05(a)(7) እና (b)(12))፣ በ 2020ው የኮሮናቫይረስ ድጋፍ የኮንግሬስ ግምገማ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማሻሸያ ህግ መሰረት፣ ከ ጁን 8፣ 2020 ጀምሮ ተፈጻሚ ከሚሆነው፣ D.C. ህግ 23-328፣ የ 2020ው የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ባለስልጣን ተጨማሪ ማራዘሚያ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማሻሸያ ህግ፣ ከ አክቶበር 5፣ 2020 ጀምሮ ተፈጻሚ የሚሆነው፣ D.C. ህግ 23-411፣ እና የከንቲባ ትዕዛዝ 2020-127 መሰረት በተሰጠኝ ስልጣን፣በቀን ዲሴምበር 18፣ 2020፣ እነሆ **ታዟል፥**

የኮሮናቫይረስ (COVID-19) ስርጭት ስጋቶችን ለመፍታት ከወጣው የከንቲባው የአስቸኳይ ጊዜ እና የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር በሚጣጣም መልኩ የ OAH አሰራሮች ከታች እንደተገለጸው ተስተካክለዋል ። OAH ሁኔታዎች በሚጠይቁት መሰረት እና ከንቲባው ለD.C. የመንግስት ኤጀንሲዎች በሚሰጡት ትእዛዝ መሰረት ተጨማሪ ማስተካከያዎችን ያደርጋል።

የሚከተሉት አሰራሮች እስከ ሜይ 31፣ 2021 ድረስ ተፈጻሚ ናቸው፥

## I. ክርክሮች

ሌላ ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ በአካል የሚደረጉ ሁሉም ክርክሮች ተሰርዘዋል። ባሁን ጊዜ ጥቅም ላይ ያሉ፣ በርቀት በስልክ የሚደረጉ ችሎቶች፣ ወደ ፊትም ለሁሉም ጉዳዮች መደረጋቸውን ይቀጥላሉ፣ ከ ህዝብ ሥራዎች መምሪያ እና የኪራይ ተሸከርካሪዎች መምሪያ በስተቀር። በርቀት በስልክ የሚደረጉ ችሎቶች በ 2021 ውስጥ ለ ህዝብ ሥራዎች መምሪያ እና የኪራይ ተሽከርካሪዎች መምሪያ ተመልሶ ይጀመራሉ። እየመራ ባለው የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ምርጫ፣ የቪድዮ ችሎቶች በ ጉዳይ-በ-ጉዳይ መሰረት የጊዜ ሰሌዳ ሊወጣላቸው ይችላል፣ የሁሉም አካላት ፍትህ፣ የችሎቱ አካሄዶች ሁኔታ፣ እና የማስረጃ ውስብስብነትን በማመዛዘን። ሌሎች ሁሉም ጉዳዮች ሌላ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ ቀጠሮ አይሰጣቸውም። ሁሉም የተሰረዙ በአካል ወይም በርቀት በስልክ የሚደረጉ ክርክሮች፣ የተለወጠው የቀጠሮ ጊዜ የሚያሳይ ትእዛዝ ለተከራካሪ ወገኖች ይላክላቸዋል።

ሁሉም የተሰረዙ በአካል ወይም በርቀት በስልክ የሚደረጉ ክርክሮች፣ የተለወጠው የቀጠሮ ጊዜ የሚያሳይ ትእዛዝ ለተከራካሪ ወገኖች ይላክላቸዋል።

## II. 441 Fourth Street, NW, Suite 450N Closure

በ 441 Fourth Street፣ NW፣ Suite 450N የሚገኘው የ OAH ቢሮ ተጨማሪ ማስታወቂያ እስከሚወጣ ድረስ መዘጋቱን ይቀጥላል። ከንቲባው ሁሉም የOAH ሰራዎች በርቀት እንዲከናወኑ ስለወሰነ፣ ወደ ህንጻው የተወሰኑ ሰራተኞች ብቻ እንዲገቡ

ይፈቀዳል። ከታች ባለው ክፍል 4 ውስጥ እንደ ተብራራው፣ OAH በ ኤሌክትሮኒክስ፣ በፋክስ፣ እና በፖስታ የሚላኩ ሁሉም ሰነዶችን አሁንም ይቀበላል እናም ያያል፣ ምንም እንኳ በፖስታ መላክ የተወሰነ መዘግየትን ሊያስከትል ቢችልም።

## III. ፋይል የማድረጊያ የመጨረሻ የጊዜ ገደቦችን ማገድ/ማዘግየት/ ማራዘም

<u>**ሁሉም ፋይል ማድረጊያ የመጨረሻ የጊዜ ገደቦች ለሚከተሉት የጉዳይ ዓይነቶች ለህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቆይታ ጊዜ እና የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ማለቅን ተከትሎ ላሉት ሰላሳ የካሌንደር ቀናት የታገዱ/የዘገዩ/የተራዘሙ ይሆናሉ፥**</u>

- የስራ አጥነት መድን (DOES)
- አጠቃላይ የህጻናት እርዳታ (DHS)
- ታንፍ (TANF) (DHS)
- ጊዚያዊ የአካል ጉድለት እርዳታ (DHS)
- Power on Work, Employment, and Responsibility (ፓወር የስራ፣ የቅጥር፣ እና የሃላፊነት) (DHS)
- ለቤት አልባ ሰዎች መጠለያ እና አገልግሎቶች (DHS)
- የቤት ኪራይ እርዳታ ፕሮግራሞች (DHS)
- የልጅ እንክብካቤ የድጎማ ፕሮግራሞች(OSSE)
- የስነቀብር ድጋፍ (DHS)
- አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤቶች የሀይል እርዳታ ፕሮግራም(LIHEAP) (DOEE)
- የሞያ የተሃድሶ አገልግሎቶች (DDS)
- የነርሲንግ ቤት ተቋም የኗሪዎች ይግባኞች (DOH)
- የአእምሮ ጤና የማህበረሰብ መኖሪያ ተቋም የኗሪ ይግባኞች (DBH)
- ራንዶልፍ-ሼፓርድ የአይነ-ስውር ሻጭ ፕሮግራም (DDS)
- የልጅ ድጋፍ ግዴታ ያለበት ሰው ገንዘብ ስምምነትን በግል ጉዳት ወይም በሰራተኛ የካሳ አቤቱታ (OAG) ላይ ማያያዝ
- የልጅ ድጋፍ ግዴታ ባለበት ሰው የተያዙ እና በፋይናንስ ተቋማት የተያዙ ገንዘቦች እንዲታገዱ እና እንዲያዙ የሚቀርቡ

ጥያቄዎች (OAG)

- የልጅ ድጋፍ ግዴታ ያለበት ሰው የመንጃ ፍቃድ መከልከል፣ እድሳት መከልከል፣ ወይም መታገድ እና የመኪና ምዝገባ (OAG)

በሌሎች አይነት ጉዳዮች ፋይል የማቅረቢያ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ እንደየጉዳዩ አይነት በተናጠል በዋና የአስተዳደርግ ህግ ዳኛ ትእዛዝ ሊታገድ/ሊዘገይ/ሊራዘም ይችላል። የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ሲያበቃ፣ ዋና የአስተዳደር ህግ ዳኛ የእገዳ/መዘግየት/መራዘም የጊዜ ወሰን እንዲያበቃ የሚያደርግ ትእዛዝ ያስተላልፋሉ እና ተከራካሪ ወገኖች ፋይላቸውን ለማቅረብ ሰላሳ ቀናት ይኖራቸዋል። ይህ ከላይ ለተገለጹት አይነት ጉዳዮች ለ OAH ፋይል የተደረገ ማንኛውም ክርክር እንዲሰማ የሚቀርብ ክስ፣ አቤቱታ፣ ኤግዝቢት፣ የምስክር ዝርዝር፣ ወይም ማንኛውም የጽሁፍ ማመልከቻ ፋይል ከማድረግ ጋር ለተያያዙት ሁሉም የመጨረሻ የጊዜ ገደብ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## IV. አዲስ የሚከፈቱ ፋይሎች

OAH አዲስ የሚቀርቡ ፋይሎችን በኢሜይል፣ በፖስታ፣ እና ፋክስ ሊቀበል ይችላል። ይሁን እንጂ፣ በፖስታ ፋይል ማድረግ መዘግየትን ሊያስከትል ስለሚችል በኤሌክትሮኒክ ስ እና በፋክስ ፋይል ማድረግ በጥብቅ ይበረታታል። ሰነድ ኤሌክትሮኒክ በሆነ መንገድ ለ OAH ፋይል ለማድረግ፣ ተከራካሪ ወገን ወደoah.filing@dc.gov ኢሜይል ማድረግ አለበት። በOAH ደንብ 2809.4 ውስጥ እንደቀረበ ከሆነ በስተቀር፣ በመደበኛ የሥራ ሰዓታት፣ ይህም ከጥዋቱ 9፡00 እስከ ከሰዓት 5፡00፣ በሥራ ቀናት የተቀበለ ሰነድ በዚያው ቀን ፋይል ይደረጋል። ከመደበኛ የስራ ሰዓታት ውጪ የመጣ ሰነድ ፋይል የማድረጊያ ጊዜ ቀጥሎ ባለው መደበኛ የስራ ቀን ነው። ማንኛውም በኢሜይል ፋይል የተደረገ ሰነድ የ OAH መመሪያ 2841 መተግበር አለበት። በ OAH መመሪያ 2971 ላይ እንደተመለከተው፣ የህዝብ ጥቅማጥቅም ጉዳዮች ላይ ክርክር እንዲሰማ በስልክ መጠየቅም ይቻላል። ጥያቄዎች ለ202-671-0055 ሊቀርቡ ይገባል።

***<u>ያስተውሉ፥ ከላይ እንደተገለፀው፣ ሁሉም ፋይል ማድረጊያ የመጨረሻ የጊዜ ገደቦች በክፍል 3 ውስጥ ለተለዩ ጉዳዮች ለህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቆይታ ጊዜ እና የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ማለቅን ተከትሎ ላሉት ሰላሳ  የካሌንደር ቀናት የታገዱ/የዘገዩ/የተራዘሙ ይሆናሉ።</u>***

## V. የዳግም ዳኝነት ፣ አዲስ ክርክር፣ ወይም የመጨረሻ ትእዛዝ እንዲስተካከል ስለመጠየቅ

የዳግም ዳኝነት፣ አዲስ ችሎት፣ ወይም የመጨረሻ ትእዛዝ እንዲስተካከል የሚቀርብ አቤቱታ ላይ የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛው ትእዛዝ ሊሰጥበት የሚገባው የጊዜ ወሰን የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ባለበት ወቅት እና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ማብቃቱብ ተከትሎ ላሉት ሰላሳ የካሌንደር ቀናት የታገደ/የዘገየ/የተራዘመ ይሆናል። በዚህ ወቅት ALJ ተፈጻሚ የሆነ ትእዛዝ ያልሰጠበት ማንኛውም የዳግም ዳኝነት፣ አዲስ ክርክር፣ ወይም የመጨረሻ ትእዛዝ እንዲስተካከል የሚቀርብ አቤቱታ እንዳልተከለከለ ወይም በህግ መሰረት እንዳልተከለከለ ይቆጠራል።

በኦገስት 27, 2020 ላይ የወጣው የDCCA ትዕዛዝ መሠረት፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአቤቱታ ሰሚ ፍርድ ቤት ከእንግዲህ የፋይል ማድረጊያ የመጨረሻ ቀነ-ገደቦችን እያገደ ወይም እየዘገየ እንዳልሆነ እባክዎ ያስተውሉ። ለረቂቆች፣ ገለፃዎች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ ፋይሎችን አስመልክቶ የጊዜ ርዝመትን የሚጠይቁ ረቂቆች በጉዳይ ፍትህ ጋር እንዲመጣጠን በነፃነት ተሰጥቷል።

## VI. በአጭር ስነስርአት የሚቀርብ የክስ አቤቱታዎች

OAH የተከራካሪ ወገኖችን ክርክሮች እና በአጭር ስነስርአት በሚቀርብ አቤቱታዎች መሰረት ጉዳዮችን ማየት እና መወሰኑን ይቀጥላል። በደብዳቤ ወይም በፋክስ ፋይል ማድረግ መዘግየትን የሚያስከትል በመሆኑ፣ ክርክሮች እና ጊዜያዊ የአቤቱታ ጥያቄዎች

## VII. ግልግሎች

ባለፈው ከወጣ ህግ ወዲህ፣ OAH የተወሰኑ ጉዳዮች ውስጥ ሽምግልናዎችን መልሶ ጀምሯል። የተላለፉ ሽምግልናዎች እንዳስፈላጊነቱ ለያንዳንዱ ጉዳይ እየመራ ባለው የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ቀጠሮ መያዛቸውን ወይም እንደገና ቀጠሮ መያዛቸውን ይቀጥላሉ።

ወንድ ኮሊን ኩሪ
ዋና የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ተወካይ

December 30, 2020
ቀን



በዚህ ወቅት ስለይግባኝዎ ያሉት ጥያቄዎች ወደ (202) 442-9094 ወይም

oah.filing@dc.gov ይመራሉ።